ጥቅምት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓ. ም.

ለተከበሩ አቶ ዘውዱ ተፈራ፤
በደቡብ ጎንደር መስተዳድር፣ በላይ ጋይንት ወረዳ፤
የቀበሌ ፳፫ ዋና አስተዳዳሪ፤

<u>ሰኞ ገበያ።</u>

እኛ፡ በዚህ በቀበሌ ፳፫ (ሃያ ሦስት) ውስጥ የምንገኝ ነዋሪዎች፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ ለክቡርነትዎ እናመለክታለን።

ይኸውም፡ ከሰባቱ ሰበካ ጉባኤዎች ተመርጠንና ተወክለን፡ ከጥቅምት ፩ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. ጀምሮ፡ በአለቃ ዘካርያስ ስም፡ አንድ የኅብረት ልማት እንቅስቃሴን አቋቁመን የምንሠራ መኾናችንን የሚመለከት ነው። በዚህ መሠረት፡ የቀበሌያችን ነዋሪዎች ከኾኑት፡ ከእየሰበካ ጉባኤዎቻችን አባሎች ባሰባሰብነው፥ ደግሞም፡ ከአለቃ ዘካርያስ ተወላጆች ባገኘነው የገንዘብ፥ የቍሳቍስና የጉልበት አስተዋጽኦ፡ የልማቱን ሥራ፡ እስካኹን፡ ዓቅማችን በፈቀደ፡ በኅብረት ስናካኺድ ቆይተናል፤ አኹንም፡ እያካኼድን እንገኛለን።

ይኹን እንጂ፡ በኅብረት የምንሠራው፡ ይኸው የልማት እንቅስቃሴያችን፡ እያደገና እየተጠናከረ ከመኼዱ የተነሣ፥ በተለይም፡ ለወደፊቱ ያቀድነውን መጠነ ሰፊና ዘርፈ ብዙ የኾነውን የልማት ሥራችንን፡ በበለጠ ቅንብርና ቅልጥፍና፡ በተግባር ላይ ለማዋል ይቻለን ዘንድ፡ የዚሁ እንቅስቃሴያችን ማቋቋሚያና መመሪያ የኾነው ሥርዓታችን፡ በወረዳው አስተዳደር ዘንድ ታውቆ ሊመዘገብልን የሚያስፈልግ ኾኖ አግኝተነዋል።

ስለዚህ፡ "በኢትዮጵያ፡ እመ ሀገር፣ የአለቃ ዘካርያስ፥ ንዋየ ክርስቶስ መታሰቢያ ድርጅት።" የሚል ስያሜን የሰጠነው፡ የዚሁ ድርጅታችን፡ ማቋቋሚያው እና መመሪያው የኾነውን ሥርዓት የያዘው፡ ባለሃያ አንድ ገጽ ጽሑፍ፡ ይጸድቅልን ዘንድ፡ ታኅሣሥ ፲፮ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. የተጻፈውን ዐባሪውን ደብዳቤ ጭምር፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ፡ ለክቡርነትዎ አቅርበናል።

በዚህ አጋጣሚም፡ "የሰኞ ገበያ" የሚለው የከተማችን ስም፡ "የዘካርያስ ከተማ" በሚለው ስያሜ እንዲለወጥ፡ ከዚህ ቀደም ያመለከትነው ታውሶ፡ ይኸው ተስማምተንበት እየጠራንበት ያለው ስያሜ እንዲጸና ያደርጉልን ዘንድ፡ በትሕትና ስናስታውስዎ፡ ጥያቄዎቻችን ተቀባይነትን እንደሚያገኙልን በመተማመን ነው።

በአመልካቾች ስም፡-